# የቅማንት ኮሚቴ ወንጀሎችና የአዴፓ መንታ ምላስ

" ከ 600 መቶ ዓመት በፊት ከአካለጉዛይና አዲግራት አካባቢ ተነስተን ጎንደር ላይ ሰፍረናል" የሚል ታሪካዊ ትንተና ይዞ ብቅ ያለው ጨካኙ የቅማንት ኮሚቴ በራሱ አንደበት በአማራው አገር ላይ መጤ መሆኑን በማያሻማና በማያከራክር ሁኔታ የማንነቱን ሀቅ ባደባባይ አፍረጥርጦታል። አማራዎች ደግሞ " ከቅማንት ጋር ለረጅም ዘመናት መሬታችንን አካፍለን ሰጥተን፤ ተጋብተንና ተዋልደን፤ በክፉና ደጉ ነገር ሁሉ ባንድነት እኩል ተካፍለንና ተዋህደን አብረን ኖረናል።" በሚል ትርክት የአማራ ሕዝብ ዋነኛ መገለጫ የሆነውን እንግዳ ተቀባይነት፤ ባይተዋሮችን እንደራሱ የመቁጠርንና በሰላም ተቻችሎና ተከባብሮ መኖርን ትላንትም ሆነ ዛሬ ከመተግበር ወደ ሁዋላ ያለበት ግዜ ፈፅሞ የለም። " አማራ የዋህ ነው" የሚል አገላለጽ በሌሎች ወገኖችም የሚሰጥበት ምክንያቱ ይህ አቃፊና ታጋሽ ባህሉ እንደሆነ ትክ ብሎ ነገሩን ላጤነው አባባሉን ለመረዳት የሚያስቸግር አይደለም።

ኮሚቴው በይፋ መንቀሳቀስ ከጀመረበት ወቅት አንስቶ ማን እንደመሰረተው፤ የገንዘብና ሌላም ድጋፍ ለምሳሌ የወታደራዊ ስልጠናና ትጥቅ እንደዚሁም የፖለቲካ ድጋፍ የሚቸረው ሕወሐት ለመሆኑ ምንም የተደበቀ ነገር የለም። የፌደሬሽን ምክር ቤት በብአዴኖቹ ካሳ ተ/ብርሀንና ያለው አባተ ሲመራ ቅማንት ከአማራ በቋንቋና ስነልቦና የተለየና በኩታ ገጠም በታች አርማጭሆና ጎንደር ዙሪያ ወዘተ ያለ ማህበረሰብ ስለሆነ በሚል ወያኔያዊ ትንተና ብቻ ራሱን የቻለ ብሔረሰብ ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተደረገ። የአማራ ወኪልና መሪ ነኝ የሚለው ያሁኑ አዴፓ ሴራ መሰረቱ የሚቋጨው በዚህ ውሳኔ ላይ መሆኑንን እያንዳንዱ አማራ ሊያውቀው ይገባል። ከዚህ ቀጥሎ በጥላሸትነቱ የምናውቀው ብአዴን ያሁኑ አዴፓ ባህርዳር ባለው የደነዘዘ ምክርቤት ሰብስቦ 42 ቀበሌዎችን ያቀፈ ሰፊ መሬት ከጎንደር በመቁረስ የልዩ አስተዳደር በማዋቀር ለቅማንት ኮሚቴ ስር የሰደደ ዋንጫ አበረከተለት። ዞሮ ዞሮ መታወቅ ያለበት እውነታ አሁን በጎንደር ባለው የተወሳሰበ ችግር ተጠያቂው አዴፓ ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ ለማቅረብም ችግር የለም።

በእንክብካቤ ሳቢያ ሆዱ የሰፋን ሰው ማጥገብ እንደማይቻለው በወያኔ ከልክ ያለፈ ዘርፈ ብዙ ድጋፍ የተሰጠው የቅማንት ኮሚቴ ጎንደር ከተማን አካሎ በቆራና መተማም ተጨማሪ ሰፊ የአማራን መሬት ለመዝረፍ በገሀድ በጎንደር አማራ ላይ ጦርነት እስከማወጅ ደረሰ። አማራዎችን ከትክል ድንጋይ እስከማባረርና በየቀበሌው በመንቀሳቀስ በአማራው ላይ ነጻ ግድያ፤ ዝርፊያ፤ ሴቶችን አስገድዶ መድፈር፤ ቤቶችን እስከማቃጠል ደረሰ። ይህ ሁሉ ሲሆን ልዩ ሀይል፤ ፖሊስና ሚሊሺያ ያለው አዴፓ ኮቴውን አጥፍቶ ጭጭ ምንጭጭ በማለት አማራውን ትጥቅ እያስፈታ በቅማንት ኮሚቴ ታጣቂዎች አስፈጀው። የዚህ የጉዶች ጉድ የሆነ ድርጅት ሀጢያት በዚህ አላበቃም። የጎንደር አማራን አፍንጫህን ላስ በማለት 27 ተጨማሪ ቀበሌዎችን በራሱ ምክር ቤት የተላለፈውን የግዛት ሽንሽና ተላልፎ በማን አለብኝነት ሰጠ። አማራው በራሱ መሬት ባይተዋር ተደርጎ 69 ቀበሌዎችን ያካተተ የቅማንት ልዩ ዞን ተፈጠረ።

ቅማንትን ተንተርሶ የሚሰራው የወያኔን ማኒፌስቶ እውን ለማድረግ ስለሆነ የፌደራል መንግስት የሚባለውም በፌዴሬሽን ም/ቤት፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማሪያም ደሳለኝና ወያኔ በሚዘውረውና በሚያስተዳድረው የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አማራው እንደጥፋተኛ ቅማንት ደግሞ በደል የደረሰበት

ተደርጎ ሪፖርቶችና ፀረ አማራ ፕሮፓጋንዳ በስፋት ባለፉት አራትና ሶስት ዓመቶች ተሰርተውበታል። በዚህ ሁሉ አማራን የማዳከምና የማጥፋት ሴራ አዴፓ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንባር ቀደም የሆነ ተሳታፊነት ነበረው። በውጪ አገር ያሉ አክቲቪስቶች እንደዚሁም ጥቂት በአገር ቤት ያሉ ተቆርቋሪዎች አማራው ላይ የሚደርሰው መፈናቀልና ጭፍጨፋ በሌሎች ክልሎች ብቻ ሳይሆን በጎንደርም በግልጽ እንደሚፈፀም ሲያጋልጡ በነበረበት ግዜ አዴፓ ቅማንቶች መሳሪያቸውን እንደታጠቁና የሚያደርሱትም በደል እንዲቀጥል በዝምታ ሲያልፋቸው በአማራ ተጋድሎ ነፍጥ ያነሱትን ቁራጥ አማራዎች ከወያኔ ጋር በመሆን የገቡበት እየገባ አሳዶ እንዲሙቱ ያለ የሌለ ሀይሉን ሲጠቀም እንደነብር ሁሉም አማራ በግልጽ ያውቀዋል።

በዚህ አስከፊ ወቅት ሶሮቃ ላይ አባይ ወልዱና ገዱ አንዳርጋቸው በአማራና ትግራይ ክልሎች መካከል ያውን የድንበር ቁርሾ ፈተነዋል በሚል የአጥፍቶ ጠፊ ፖለቲካ በተፈራረሙት የድንበር ስምምነት ግጨውና አካባቢውን አዴፓ ለትግራይ በይፋ ማስረከቡን የአማራ ቴለቪዥን በምስል የተደገፈ ቀዳሚ ዜና ሰርቶ አቅርቦበታል። ለመሆኑ ይህ እኩይና ጸረ አማራ ሴራን የሚያስታውስ አማራ ይኖራል? ይህን ያልኩበት ምክንያቱ በአሜሪካ በመዘዋወር ላይ ባለው የአዴፓ የልኡካን ቡድን በጉዳዩ ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሲነሳ ባለመስማቴ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በቅርቡ ማንንም ከመጤፍ የማይቆጥረውና በትዕቢት የተወጠረው የአክራሪ ትግሬዎች ቅጥረኛ የሆነው የቅማንት ኮሚቴ በጭልጋ ወረዳ ያደረሰውን ዘግናኝ ጥፋት አማራ ምን ግዜም አይረሳውም። ከባህርዳር በቅርብ ርቀት ጎንደር ውስጥ አማራዎች በአውሬዎቹ የቅማንት ኮሚቴ ታጣቂዎች ሲጨፈጨፉና ባገራቸው ሲፈናቀሉ መቀሌ ላይ ከበሮ ሲደለቅ አዴፓዎች አማራው ራሱን እንዳይከላከል ሁለገብ አፈናዎችን በአማራው ላይ ያካሂዳሉ። በዚህ ጉዳይ አዴፓ እኛ አማራዎችን በጅቦች ማስበላትን ማቆም ካልቻለ ለህልውናችን ጠንቅና ጋሬጣ ስለሚሆን ከስልጣኑ መነሳት ይኖርበታል።

አዴፓን ወይም ብአዴን የሚባለውን የወያኔ ቡችላ የሚመሩት ሰዎች አሁንም አስተሳሰባቸው ከሕወሐት ዓላማ ውጪ ነው ብሎ ለመቀበል በጣም ያስቸግራል። አቶ ገዱ አንዳርጋቸው በአሜሪካ አማራውን እያወያዩ ባሉበት ወቅት በሲአትል እቅጩን እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል " እኔና አምባቸው ትግሉን የተቀላቀልንው አንድ አካባቢ ነው። ሁላችንም አምነንበት ነው የትግሉ አካል የሆንው. . ." ይህን አነጋገር ማንም በትኩረት የተመለከተው ያለ አይመስለኝም። ጎንደር ላይ ደግሞ ደመቀ መኮንን በዛሬዋ ታህሳስ 5 ቀን በተደረገው ስብሰባ ላይ ". . . የሕዝብ የማንነት ጥያቄዎች ባፋጣኝ መመለስ ይኖርባቸዋል። በጉዳዩ አሁን ላይ የአማራና ቅማንት ሕዝቦች እያልን እንድንናገር ተገደናል የነርሱም ጥያቄ መፈታት አለበት። " 69 ቀበሌዎች የቅማንት ኮሚቴ ተሸልሞ እያለ እንደገና ጥያቄው መፈታት አለበት ብሎ መናገር ምን ማለት ይሆን? እነዚህ አዴፓዎች ባንድ በኩል ተለወጥን እያሉ ዞር ብለው ደግሞ አማራውን የማጥፋቱን ስራ ያከናውናሉ። ለምሳሌ በዚሁ ስብሰባ በኢቲቪ በተላለፈው የታህሳስ 5 ዜና አቶ ደመቀ የአማራ ወላጆች ልጆቻቸውን ምከሩ እስከማለት መድረሱ ተዘግቦዋል። በጣም የሚዘገንነው ራሱ የአማራ መገናኛ ብዙሀን በጭልጋ ከሰሞኑ በተቀሰቀሰው 'ግጭት' ከ 50 በላይ ሰዎች ሞተዋል፤ ከ 500 በላይ የሆኑ ቤቶች ተቃጥለዋል እንደዚሁም 30000 (ሰላሳ ሺህ) ሰዎች ከቄያቸው ተፈናቅለዋል ሲል ቢገልፅም አቶ ደመቀም ሆነ ሌሎቹ አዴፓዎች ይህ ሁሉ ጥፋትና በደል የደረሰው እኩል በአማራውም ሆነ በቅማንት ላይ እንደሆነ አድርገው ማቅረባቸው ማንነታቸውን ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

አማራው ራሱን የሚከላከልበት መሳሪያውን እነ ደመቀ ነጥቀውት ባለበት ሁኔታ የቅማንት ኮሚቴ እስከ አፍንጫው ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ታጥቆና ዩኒፎርም የለበሱ ወታደሮች አሰልፎ አማራውን ሲገልና ሲያፈናቅል ብሎም ቤትና ንብረት አውድሞ ዝርፊያ ሲፈጽም አማራውን እኩል ከቅማንት ኮሚቴ ጋር መወንጀል ምን የሚሉት ፍርደገምድልነት አዴፓን እንደተጠናወተው መረዳት አያዳግትም። ብ/ጀነራል አሳምነው ለብቻው እውነቱን ሲያፍረጠርጠው አቶ ገዱ አሜሪካ ላይ " እኛ መሳሪያ አላስፈታንም፤ ውሸት ነው. . ." ሲሉን ጎንደር ላይ ደግሞ አቶ ደመቀ በችግሩ ሰለባ የሆነውን አማራ አብሮ ሲወነጅል ይሰማል። ለመሆኑ 27 ዓመት እናስተዳድረዋለን በሚሉት ጎንደር ሶስትና አራት ቀበሌዎች ለዛውም ጭልጋ ወረዳ ውስጥ የቅማንት ኮሚቴ ለብቻው ተቆጣጥሮ የወታደራዊ የጦር ሰፈር አድርጎ ሲንቀሳቀስ አቶ ደመቀና አቶ ገዱ በዙሪያው ያለውን አማራ መሳሪያን ከደበቅህበት አምጣ እያሉ ሲያዋክቡት ቅማንት ኮሚቴን ለምን ዝም ብለው በ እብሪት እንዲያብጥ አደረጉት? አማራው ግልፅ ሊሆንለት የሚገባው ሀቅ ወያኔ የዘራውን መርዝ የሚኮተኩተውና ወሀ የሚያጠጣው ኢ ሕ አ ዴ ግ እንደሆነና አዴፓ(ብአዴን) ደግሞ በባለቤትነት ቅማንት የሚባል ከትግራይ ጋራ የሚዋሰን አዲስ አገር ለመፍጠር የሚንቀሳቀስ ብኩንና ፀረ አማራ ቡድን መሆኑን ሳያወላውል ማወቅ አለበት። አንድን ጠላት አደብ ይገዛል በሚል ከንቱ ውዳሴ ምን ቢለማመጡት ቢያሽሞነሙኑትና ባንድ አዳራሽ ተቀምጠው ቢያወያዩት ከጥፋት ዓላማው መቀየር ግን ፈጽሞ አይቻልም

አማራው ከእንግዲህ ወዲያ ይሉንታ የሚባለውን አጥፊ ፀባይ አስወግዶ ለህልውናው ግልፅ በሆኑና በተጨባጭ አማራነትን ማጎልበትና ጥፋት ከሚነዙበት ማንኛውም ሀይሎች የሚሰነዝሩበትን ጥቃቶች የመከላከል ተፈጥሮአዊ ግዴታዎችን መጠቀም ይኖርብርታል። 27 ዓመት ሙሉ የተጨፈጨፈ፤ መጤ ተብሎ የተፈናቀለና አሁንም የሚፈናቀል፤ ከዓመት ዓመት ለቅሶና ሙሾ በባዶ ሜዳ የሚያሰማውና አድማጭ ያጣው የአማራ ሕዝብ አዴፓም ሆነ ኢሕአዴግ አንድም ቀን በዚህ ሁሉ ዓመት ዋይታውን ሊሰሙትና ሕጋዊ መብቶቹን ሊያስከብሩለት ፈፅሞውን ፈቃደኛ ሊሆኑ አለመፍቀዳቸውን አምኖ መቀበል ይኖርበታል። ይህንን መሬት ላይ ያለ ሀቅ ብቻ መሰረት በማድረግ አማራው ባለው አቅሙ ተጠቅሞ ራሱን ለማዳን ሲል የመከላከል እርምጃ መውሰድ መጀመር ግድ የሚለው ሰዓት ላይ የተደረሰ ይመስለኛል። ሁል ግዜ ሰሚ የለሽ ለቅሶና ማንም ዞር ብሎ ለማያየው የድረሱልኝ ጥሪ ማቅረብ አቁሞ አማራው ራሱን መታደግ መጀመር አለበት። ኢትዮጵያ ውስጥ ባሁኑ ግዜ በራሱ አገር ለዛውም ከቅም ቅም ዓያቶቹ የተረከበውን መሬት የሚቀማውና የሚፈናቀለው አማራው ብቻ ነው። የጎንደር አማራ እንዴት ከጎንደር ደሙ እየፈሰሰና ቤት ንብረቱ እየወደመ ይፈናቀላል ለሰሚም ግር ይላል። ወያኔ ከመጣ አንስቶ ሁመራ፤ ወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምት ከቋራና መተማም ወደ ሱዳን መሬቶቹን የገበረው የጎንደር አማራ አሁን ደግሞ ትግራይ በቅማንት ሽፋን ሰፊ መሬት አገኘች። ከአለፋ ጣቁሳም ቆላማው ሰፊ መሬት ተቆርሶ ጃዊ ተብሎ ሄደ፤ በዚህ ሁኔታ እንዲቀጥል ከተደረገ የጎንደር አማራ የመኖርና ያለመኖር ዕጣ ፋንታ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ይህ ሁሉ ጥፋት የብ አ ዴ ን (አዴፓ) ወያኔያዊ የተልዕኮ ስራ እንደሆነ በግሌ አምናለሁ።
አብነት ሁነኛው ነኝ!